# ለኢሮብ ወጣቶች ስደት ሶስቱ ዓበይት ምክንያቶች::

## ከሱመ

## መግቢያ፤

በቅር ጊዜ የወጣው ኢሮብማብሎ የሚባል ድረ-ገጽ መከታተል ከጀመሩት የኢሮብ ተወላጆች አንዱ ነኝ። ይህ በኢሮብ ጉዳይ ላይ ያነጣጠረ፣ልንወያይበት፣ ብሶታችንን ልንገልጽበት፣ መረጃዎችን ልንለዋወጥበት፣ ልንሰባሰብበትና ልንማማርበት የምንችል መድረክ በማጣታችን እስከዛሬ እንደተበታተን በየግላችን እህህ እንዳለን ኖረናል ።አሁን ግን ዘግይቶም ቢሆን ይህ የኢሮብ ልጆች መገናኛና መወያያ መድረክ በመሆን ሊያገለግለን የምችል ድረ-ገጽ መከፈቱ ጥሩ ጅማሮ ነው። ስለሆነም የራስ አነሳሽነትን በመውሰድ ይህንን የመገናኛ፣ የመወያያና የመረጃ መለዋወጫ ድረ-ገጽ የከፈቱልን IRAA በሚል ስም የተሰባሰቡ ወገኖች መመስገን ያለባቸው ናቸው። ከድረ-ገጹ መሰረታዊ ዓመዶች አንዱ በሆነው our mission ስር የተቀመጡ መሰረታዊ የድረ-ገጹ ዓላማዎች ሁሉንም ዓይነት ሃሳቦች የሚያስተናግዱ ሆነው ስላገኘሁዋቸው በራሴ በኩል ወድጃቸዋለሁ። ዓላማዎቹ ሳይለወጡ፣ የተለያዩ ሃሳቦች በነጻ የሚስተናገዱበት ድረ-ገጽ ሆኖ እንደሚቀጥልም ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ።

ሌላም About us በሚለው ዓምድ ስር የIRAA መሰረታዊ ዓላማዎች ተቀምጠዋል። ይህ መደረጉም ጥሩ ነው። እያንዳንዱ ስለ IRAA ማንነት ማወቅ የሚፈልግ/የምትፈልግ በቀላሉ IRAA የቆመለትን ዓላማዎች ለማየት ያስችላል። ሆኖም ግን IRAA ስለ ራሱ ገና ብዙ ማስተዋወቅ እንዳለበት፣ እንግልዝኛ ለማንበብ ለማይችሉም ስለምንነቱ በሀገራችን ቋንቋዎችም ማስተዋወቅ እንዳለበት መዘንጋት የለበትም እላሎሁ። ከዚህ በተጨማሪም እያንዳንዱ/ዷ እነዚህ የIRAA ዓላማዎችን በሚገባ ተመልክቶ/ታ መተቸት ያለባቸውን እንዲተቹ መስተካከል ያለባቸው ካሉም እንዲስተካከሉ መቻል አለበት፣ IRAAም ይህንን እንዲቀበል ለማበረታታት እፈልጋለሁ። በዚህ መሰረትም IRAA የሁላችን ሆኖ እንዲቀጥል በመቀላቀል ልናጠናክረውና ልናሰፋው ይገባል እላለሁ። እንዲህ ከሆነ ብቻ ነው አሁን እንደ ኢሮብ ህልውናችንን አደጋ ላይ እያስገቡ ያሉት ችግሮችን ለመከላከል የምንችለው፣ እየደረሱብን ያሉ ሰብአዊና የማንነት መግለጫችን የሆኑ መብቶቻችንን ለማስከበር የምንችለው፣ ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ለመብታችን ለመከራከር የምንችለው የራሳችን የሆነ የተደራጀ ሃይል ሲኖረን ብቻ ነው።

ሌላ እስካሁን ድረስ በድረ-ገጹ የወጡትን የተለያዩ አርቲክሎች መልሼ መላልሼ ተመልክቻቸዋለሁ። በአጠቃላይ መልኩ ሲታይም ጥሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ይህ ዓይነት ነጻ መድረክ እንዲያድግና እንዲጠናከር ደግሞ የሁሉም ገንቢ ተሳትፎ መኖር አሰስፈላጊ መሆኑን በሚገባ አምንበታለሁ። ስለሆነም በዚሁ እምነቴ መሰረት ለዛሬ ሁሉም ኢንዲያውቃቸውና አስቸኳይ መፍትሄ እንዲፈለግለት ይገባል ብዬ ያመንኩበት የኢሮብ ወጣቶች ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የማውቀውን ያህል ለሁሉም ለማካፈል እሞክራለሁ።

ወደ መሰረታዊ ነጥቦቼ ከመግባቴ በፊት ግን ስለ ራሴ ባጭሩ ላሳውቃችሁ። እኔ የዚህ መጣጥፍ ጸሃፊ በ30ዎቹ የመጨረሻ አጋማሽ ዕድሜ ካሉት የኢሮብ ወጣቶች አንዱ ነኝ። በተጨማሪ በአከባቢያችን ሰፍኖ ያለው ሰውሰራሽና ተፈጥሮአዊ ዘርፈ ብዙ ችግር

አስመርሮአቸው፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው በአካባቢው በሰላምና በነጻነት በሞያቸው ሰርተው ለመኖር ስላልቻሉ ሀገራቸውን ጥለው ከተሰደዱት የኢሮብ ተወላጆች አንዱ ነኝ።ስለ ማንነቴና የስደቴ ምክንያት በዝርዝር ማወቅ ካስፈለገ ሌላ ጊዜ በስፋት ልመለስበት ስለምችል ለዛሬው በዚሁ አበቃለሁ።

ውድ ወገኖች፣ እኔ ከምታዘበውና ከማየው በመነሳት፣ የኢሮብ ወጣቶች ፍልሰት እንደዚህ አሁን እየሄደበት ባለው ሁኔታ ከቀጠለ፣ የኢሮብ ወጣት በኢሮብነቱ ላይ ተስፋ የመቆረጥ አደጋን ሊያስከትል ይችላል፣ የኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልውናም በከፍተኛ አደጋ ውስጥ ይገባል ባይ ነኝ። እንደኔ እምነት እንደ አንድ አናሳ ብሄረሰብ፤ አባቶቻችን ያቆዩልን መሬት ይዘን፣ ባህላችንንና ቋንቋችንን ጠብቀንና አስከብረን ለመቀጠል የምንችልበት ሁኔታ ህገመንግስቱ በሚፈቅድልን መሰረት ለማስከበር ካልቻልን እንደ ኢሮብ ብሄረሰብ ህልውናችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ ነው። ስለሆነም እንደ ኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ለመቀጠል በርካታ መቅረፍ የሚገባን ችግሮች ያሉ ቢሆንም ቅድሚያ መሰጠት ያለበት እየመረጥን እንድንወያይበትና መፍትሄ እንድንፈልግላቸው ይገባል ካልኩዋቸው ነጥቦች የወጣቱ ሁኔታ ከሁሉም ቅድሚያ ሰጥተን መፍትሄ ልንፈልግለት የሚገባ አንገብጋቢ ችግራችን ነው ከሚል እምነቴ በመነሳት ለወጣቶቹ ፍልሰት መሰረታዊ ምክንያት ናቸው ያልኩዋቸው ሶስት መንስኤዎች እንደምከተለው ለውይይት አቀርባለሁ።

## 1ኛ. መረን የለቀቀ ድህነት፣ የስራ ዕጦትና ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ በአካባቢው ማጣት

የኢሮብ ህዝብ የኑሮው ምንጭ እርሻና የእንስሳት ርቢ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው ሃቅ ነው። በአካባቢው ሳያቋርጥ ለብዙ ዓመታት በቀጠለው ድርቅ ምክንያት የተነሳ ዛሬ አካባቢው ወደ ምድረበዳነት መቀየሩንም ሁላችን እናወቃለን። በኢሮብ መሬትን አርሶ ከመሬት የሚገኝ የነበረው ምርት ማምረት ካቆመ፣ ህዝቡ የውጭ እርዳታ ጠባቂና ተመጽዋች ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል። ድሮ የነበረው የከብትና የፍየል ብዛትና እርባታ ዛሬ የለም። ድሮ የነበረው ከንብ የሚገኝ የነበረው የማር ምርት ዛሬ በኢሮብ መሬት የለም።

አካባቢው ከላይ ባጭሩ እንዳስቀመጥኩት ሲመስል እስካሁን በሚመለከታቸው መንግስታዊ ሆነ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ይህን በአካባቢው የተከሰተውን ችግር ለመቀየር የተደረገ እንቅስቃሴና የተወሰደ የሚታይ እርምጃ እሚገንት ነው ማለት ይቻላል። በ1983 ዓ.ም. የተወገደውን የደርግ አገዛዝ ትቼ የኢህአደግ የ20 ዓመታት አገዛዝ ጊዜ ውስጥ በኢሮብ ወረዳ የተከናወኑ የአካባቢውንና የህዝቡን ህይወት ሊቀይሩ ይችላሉ የሚባሉ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ስመለከት ያለኝ መልስም ኢሚገንት ነው የሚል ነው። ባለፉት 20 ዓመታት በአካባቢው የህዝቡን ህይወት ሊቀይር የምችል፣ ተስፋ የሚያሰጥ የተሰራ አንድ ነገር አለ ከተባለ በዶክተር ቡሩኖ የሚመራ የበጎ አድራጎት ድርጅት የሰራው የዓሳቦል የግድብ ፕሮጀክት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ሊታይ የምችል የህዝቡን ህይወት የሚቀይር፣ ለህዝቡ የስራ ዕድል የሚፈጥር፣ ተስፋ የሚሰጥ ፕሮጀክት አለ የሚል/ትል ካለ/ች ለማየት/ለመስማት ዝግጁ ነኝ። **እንደኔ እምነት ድህነት፣ በአካባቢው ተስፋ የሚያሰጥ ሁኔታ አለማየት ለበርካታ የኢሮብ ወጣቶች መሰደድ አንዱና ዋነኛ ከሚባሉ መሰረታዊ ችግሮች ውስጥ ነው። ስለሆነም ዛሬ**

<u>***የድህንት ኑሮ ያስመረራቸው፣ ዘላለም ተመጽዋች እንዲሆኑ የሚያስገድዳቸው፣ በአከባቢው ለመኖር የሚያስችል የሚታይ የወደፊት ተስፋ ባለመኖሩ የተጨነቁ፣ የኢሮብ ወጣቶች አከባቢያቸውን እየለቀቁ ለሥራና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደተለያዩ አከባቢዎች መሰደድ የግድ ሆኖባቸዋል ባይ ነኝ።***</u>

*ሌላ ዛሬ ሁላችንም ትኩረት ሰጥተን ልንወያይበትና መፍትሂ ልንፈልግለት የሚገባን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጠል ያልቻሉ፣ ትምህርታቸውን ለማሻሻል የተለያዩ ኮርሶች ለመውሰድ አቅም ያጠራቸው፣የስራ ዕድል ያላገኙ ወጣቶች ተመልሰው የድሃ ወላጆቻቸው ሸክም የመሆን ጉዳይ ነው። እነዚህ ወጣቶች ስራ ስለሌላቸው፣ ወጣቶቹን የሚያነሳሳ እንቅስቃሴ በአከባቢው ባለመኖሩ፣ ጊዜያቸውን ሊያሳልፉበት የሚችሉ ሌላ ነገር ሰለሌለ፣ እንደ ጊዜያቸው ማሳለፊያ የሚጠቀሙበት አሁን በሞላው ኢሮብ እንደ አሸን ፈልተው ያሉ መጠጥ ቤቶችን ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚያድግ ወጣት ለወደፊት ምን ሊሆን እንደምችል፣ ምን ያህል ለህብረተሰቡ ሸክም እንደሚሆን፣ እነዚህ ወጣቶች ለወደፊቱ በኢሮብነታቸው ላይ የሚኖራቸው አመለካከትና ወደፊት እንደ ጥሩ ኢሮብ ሆኖ የመቀጠል ተስፋ ምን ሊሆን እንደምችል ከወዲሁ መገመት ከባድ አይደለምና ሌላው ትልቁ ችግራችን ነው።*

*በሌላው ችግራችን የኢሮብ ወጣቶች ከላይ ባስቀምጥኩዋቸው ችግሮች ውስጥ መሆናቸውን በሚገባ የተገነዘቡና ያወቁ ከገንዘብ ውጭ ምንም ነገር የማይታያቸው ስግብግብ ነብሰባላ ነጋዴዎች ይህን ደካማ ጎን በመጠቀም ገንዘብ ሊያገኙ የምችሉትን ወጣቶች ከአከባቢው የማፍለስ ተግባር እንደ አንድ ትልቅ ንግድ መያያዛቸው ነው። እነዚህ ነጋዴዎች ከውጭ ከዘመድ አዝማድ ገንዘብ ሊያገኙ የሚችሉትን ወጣቶች በማደን ስራ ወዳለበት፣ ገንዘብ እንደልብ ወደሚገኝበት ሀገራት እንወስዳችኋለን በማለት በተደራጀ መልክ ወጣቶቹን ወደተለያየ አከባቢ በገንዘብ የማጓጓዝ ስራ እንደ አንድ ትልቅ የስራ መስክ ይዘዉት እንዳለ መንግስትም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። በዚህ መልክ ከሚደረገው የወጣቶች በገንዘብ የማፍለስ ተግባር በርካታ ወጣቶችን ወደ እስራኤል የማጓጓዝ ተግባር በዋናነት ሊጠቀሱ ከምችሉት ውስጥ አንዱ ነው። በዚህ ወደ እስራኤል ወጣቱን ለመጓጓዝ በሚደረገው ጉዞ በርካታ ወጣቶች በሲናይ በረሃ ቀልጠው ቀርተዋል፣ በርካታ እህቶቻችን በዓረቦች ተደፍረዋል፣ ተቀጥቅጠዋል፣ አሁንም እየተቀጠቀጡ ነው። ስለሆነም ይህንም እንደ ትልቁ ችግራችን ተመልክተን እነዚህ ነብሰበላ ነጋዴዎች ለህግ የሚቀርቡበት መንገድ በማመቻቸት፣ ይህንን ተግባር ለማስቆም ሁላችን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።*

*ሌላው እዚህ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ቢኖር ወደ ኤርትራ የሚኮበልሉ የኢሮብ ወጣቶችን የሚመለከት ነው። በሻዓቢያ ድጋፍ የሚንቀሳቀሰው 'ዴሞክራሲያዊ ምንቅስቓስ ህዝቢ ትግራይን' (ዴ.ም.ህ.ት) ለመቀላቀል ወደ ኤርትራ የሚኮበልሉ ወጣቶች እንዳሉ ግልጽ ነው። በኔ አመለካከት ሃያ ዓመታት በአቶ ኢሳያስ አምባገነናዊ አገዛዝ ስር የወደቀው የኤርትራ ህዝብ የሚገኝበት ሰቆቃ ዛሬ ለሁሉም ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው። የኤርትራ መንግስት ከአንድ መቶ በላይ የሚሆኑ ንጹሀን ዜጎቻችንን ወስዶ የት እንዳደረሳቸው እስከ ዛሬዋ ዕለት አይታወቅም። በመሆኑም በኤርትራ ተደግፎ ደግ ነገር ለኢሮብም ሆነ ባጠቃላይ ለኢትዮጵያ የሚያመጣ ኃይል ይኖራል ብሎ የሚገምት የኢሮብ ተወላጅ አለ ብሎ መናገር*

የሚቻል አይደለም። ይህ መሆኑ እየታወቀ የኢሮብ ወጣቶች ወደ የሻዓቢያዋ ኤርትራ መኮብለል እጅጉን የሚያሳስብ ጉዳይ ነው።

ለነዚህ ወጣቶች ወደ ኤርትራ መኮብለል የግድ አንድ ምክንያት መኖር አለበት። በእኔ እምነትና መረጃ ለኢሮብ ወጣቶችና ለዓቅመ አዳም ያልደረሱ ሕፃናት ልጆች ወደ ኤርትሪያ መኮብለል በዋናነት ተጠያቂው አሁን ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው የኢህአዴግ መንግስት ነው። ይህን የምልበት ምክንያት ደግሞ የኢህአዴግ መንግስት ለወጣቶቹ መሟላት ያለበትን ሁሉ አቅሙ በሚፈቅደው ደረጃ ቢያሟላላቸው፣ ለወደፊት የብሩህ ተስፋ ጭላንጭል የሚያሳይ ሁኔታ ቢፈጥርላቸው፣ በትክክል መኖር የሚገባው ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብታቸውን ቢጠብቅላቸው ኖሮ እነዚህ ወጣቶች ዛሬ ለዜጎቿ ገሀነም ወደ ሆነችው የዛሬቱ ኤርትራ ፈጽሞ አይሄዱም ነበር። ከእሳት ወደ ረመጥ የሆነውን ምርጫ የኢሮብ ወጣቶች ፈጽመው አይመርጡም ነበር ባይ ነኝ። ለኔ ለነዚህ ወጣቶች ወደ ደ.ም.ህ.ት መኮብለል ተጠያቂው የኢህአዴግ መንግስት ነው። ስለሆነም የኢህአዴግ መንግስት ችግራችንን በሚገባ ተገንዝቦ ለችግሩ መሰረታዊ መፍትሄ እንዲሰጥ አንድ ላይ ሆነን እንጠይቀው፤ ባይ ነኝ።

ሌላው በሁሉም ሊታወቅና አስቸኳይ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባው ችግር አንዳንድ ደ.ም.ህ.ት ተብሎ ወደሚጠራው ድርጅት ሂደው ሁኔታውን በሚገባ ከተገነዘቡ በኋላ ተመልሰው ለኢትዮጵያ መንግስት እጃቸውን በሚሰጡ ወጣቶችና ለዓቅመ ዓዳም ያልደረሱ ሕፃናት ልጆች ላይ በኢህአዴግ መንግስትና የስርዓቱ ካድሬዎች የሚፈጸሙ ኢሰብአዊ ድርጊቶችና የሚሰጠው ውሳኔ ነው። ከኤርትራ ተመልሰው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሕፃናትን ጨምሮ ብዙ ድብደባና እንግልት የደረሰባቸው የኢሮብ ወጣቶች ስለመኖራቸው ሁላችን የምናውቀው ጉዳይ ነው። ብዙዎች ላይም ከብዙ ዓመታት እስከ እድሜ ልክ እስራት ሁሉ እንደተፈረደባቸው እናውቃለን። ይህ ኢፍትሃዊ ተግባርና ውሳኔም አሁን በሻዓቢያ የተደራጀውን ደ.ም.ህ.ትን በመተው ወደ ሀገራቸው ሊመለሱ ለሚፈልጉ ወጣቶችና ሕፃናት ልጆች እንዳይመለሱ የሚያደርግ ጨካኝና ትክክል ያለሆነ ድርጊት እንደሆነም የምናውቅ እናውቀዋለን። እነዚህ የሚመለሱ ወጣቶች ለጥፋታቸው የሚመጥን ትምህርት ተሰጥቶአቸው፣ በጥሩ ሁኔታ ቢያዙና ትክክለኛ ኑሮ እንዲጀምሩ በመንግስትና በካድሬዎቹ ሁኔታው ቢመቻችላቸው ኖሮ ለወደፊትም ወጣቶች አይሄዱም ነበር፣ የሄዱትም የሚመለሱበት ሁኔታ ሊፈጥር በቻለ ነበር። ስለሆነ ይህም ሊሰመርበትና መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባው ሌላው ችግር ነው።

ሌላ አንድ በሁኔታው እንደኔ የተቃጠለ ወገን በቅርብ ጊዜ ደውሎ የዞባ ተወካዮች ወደ ኢሮብ ወረዳ በመውረድ የህዝቡ ተጠሪዎችን በዳውሃን ሰብስበው ስለእነዚህ ወደ ደ.ም.ህ.ት የሚሄዱ ወጣቶችን በተመለከተ ለወላጆች ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጡ ብሎ የነገረኝ ጉዳይ ነው። እኔ በርግጠኝነት ለመናገር የምችለው የፈለገው ነገር ቢሆን የኢሮብ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ሻዕቢያ ቅጥረኛ ወደሆነ ድርጅት እንደማይልኩ ነው። እነዚህ ልጆች ሲሄዱ ከወላጆቻቸው ጋር እየተማከሩና በነሱ እየተመረቁ እንዳልሆነ እኔም ሆንኩ የዞባው መሪዎች ነን ባዮች በሚገባና ጠንቅቀን የምናውቀው ሃቅ ነው። እንቆቅልሹ ችግሩን እያወቁት ይህን ሚስክን ህዝብ እንደዚህ ማስጨነቃቸው ላይ ነው። የዞባው መሪዎች ህዝቡን ማስፈራራትን አቁመው በችግሩ መንስኤና ችግሩን ከስር መሰረቱ ለመቅረፍ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ላይ

ከወላጆችና ከራሳቸው ከወጣቶቹ ጋር መወያየትና አብሮ መስራት ብቸኛው መፍትሄ እንደሆነ በሚገባ ተገንዝበው ይህን እንዲያደርጉ በሁላችንም መገፋት ያለበት ጉዳይ ነው።

## 2ኛ. የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ አገዛዝ በአከባቢው መስፈን።

ስለ ኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ወቅታዊ ሁኔታ ስናነሳ የኢሮብ ህዝብ ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ውጭ አንድም ቀን እንኳን ያልኖረ ህዝብ እንደሆነ በግልጽ መታወቅ አለበት። ስለሆነም የኢሮብ ህዝብ ወቅታዊ ሁኔታን ስንመለከት በአጠቃላይ በሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው መመልከት ያለብን። በዚህ መሰረት በሀገራችን ኢትዮጵያ የደርግ ፋሽሽታዊ አገዛዝ ተገርስሶ በኢህአዴግ አገዛዝ ከተተካ በኋላ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ስመለከት፣ ምንም እንኳን በአገዛዙ ካድሬዎች ዴሞክራሲ ሰፍኗል፣ የብሄረሰብ መብት ተከብሯል፣ ህገመንግስት ወጥቶ በህገመንግሰቱ መሰረት የኢትዮጵያ ህዝቦች አድገዋል፣ ሁሉም ነገር ተስተካክሏል ቢሉንም ለኔ ለውጥ አይታየኝም። እንደኔ እምነት በኢህአዴግ ስም ስልጣን ከደርግ በጠመንጃ ሃይል የተረከቡ ገዢዎቻችን ብዙ ቢሉም፣ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት በሀገራቸን ሰፍኗል ብለው ቢሰብኩም በተግባር በሀገራችን በአጠቃላይ ሆነ በአከባቢያችን/በኢሮብ ወረዳ ዛሬም ሰፍኖ ያለው ያው እንደ ደርጉ ዘመን የአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው። አከባቢያችንን ለየት አድርገን ስንመለከት ህወሓት ከመከፋፈሉ በፊት ሁሉም ነገር በህወሓት ሙሉ ቁጥጥር ስር የነበረበት፣ ከህወሓት አመራር ለሁለት መከፋፈል በኋላ ደግሞ ሁሉም ነገር ህወሓት ተሃድሶ ብሎ ራሱን በሚጠራው ቡድን ሙሉ ቁጥጥር ስር የሆነበት ሁኔታ ላይ ነው የምንገኘው።

ዛሬ በኢሮብ ወረዳም ሆነ በመላዋ ትግራይ የህወሓት ተሃድሶ አባል ወይም ደጋፊ ያለሆነ ሰው በሞያው ስራ የማግኘት ዕድሉ በጣም የጠበበ ነው። በሞያቸው የተከበሩ ግን የህወሓት ተሃድሶ አባል ለመሆን ስላልፈለጉ ብቻ ከስራ የታገዱና ሁኔታው ከአቅማቸው በላይ ሆኖባቸው የተሰደዱም እንዳሉ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ስደትን እንደ አማራጭ አንወስድም ብለው ስራፈት ሆነው እየኖሩ ያሉ እንዳሉም ሁላችን እናወቃለን። ሌላም የከፍተኛ ትምህረት ዕድል ማግኘት ባለህ ነጥብ ደረጃ ሳይሆን በፖሊቲካ አመለካከት እንደሆነ ሁላችንም እናወቃለን።

በዚህ የአንድ ፓርቲ አምባገናዊ አገዘዝ ምክንያትና በፓርቲው ካድሬዎች ከፍተኛ ተጽእኖ በርካታ ወጣት ምሁራን ከኢሮብ ብሄረሰብ ሆነ ከአጠቃላይ ኢትዮጵያ እየተሰደዱ ነው። ይህን የምለው ደግሞ ዝም ብዬ ከመሬት በመነሳት ሳይሆን በዚህ ምክንያት ከተሰደዱት አንዱ እኔው ራሴ ስለሆንኩ ይህን ችግር በሚገባ ስለማውቀው ነው። ይህ አሁን በአከባቢያችን ሆነ በአጠቃላይ በመላዋ ኢትዮጵያ ሰፍኖ ያለው የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ተወግዶ ፍትሃዊ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት በሀገራችን ካልሰፈነ የሙሁሩ ስደት እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለውም። የዚህ የተማረው ሃይል መሰደድ ደግሞ በሀገሪቷና በህዝቦቿ ዕድገትና ህልውና ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ በሚገባ ታይቶ አስቸኳይ መፍትሄ ሊፈለግለት ከሚገቡ ችግሮቻችን አንዱ ነው።

## 3ኛ.አንዳንድ የሰራዊቱ አባላት በሴቶች ላይ የሚፈጽሙት ያለፍላጎት የግብረስጋ ግኑኝነትና መዘዙ

የኢትዮጵጲያ መከላከያ ሰራዊት በአከባቢው በመስፈሩ እንዴት ለወጣት የኢሮብ ሴቶች ከአከባቢው መሰደድ መንስኤ እየሆነ እንዳለ ከመዘርዘሬ በፊት በኢህአዴግ አገዛዝ ተቀባይነት ካገኘው ከሄግ ውሳኔ በኋላ ከኤርትሪያ ጋር ድንበራችን ምን እንደሚመስል ትንሽ ለማሳየት ይፈቀድልኝ። ይህንን የማደርገው አንደኛ እወቀቱና ችሎታው ያላቸው በዚህ ጉዳይ ላይ ይበልጥ ግልጽ መሆን ያለባቸውን በግልጽ በካርታ እያስደገፉ እንድያስቀምጡና ሁሉም እንዲያውቀው እንዲያደርጉ ለማሳሰብ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ <u>አዶሓ ኢሮብ</u> እየተባለ ከሚጠራው አንደኛው ክፍል ማለት አድጋዲዓረና ብዙ መንደሮች ከቡክናቲዓረ ወደ ኤርትሪያ የተወሰዱበት ሁኔታ ላይ ስለሆን ይህ በሁሉም ጉዳዩ በሚመለከተው በግልጽ እንዲታወቅና መወሰድ ያለበት እርምጃ የድንበሩ ጉዳይ በማነኛውም በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት ካርታ ተሰርቶ በዛ መሰረት በተግባር ከመሰመሩ በፊት ማድረግ ያለብን ሁሉ እንድናደረግ ለማሳሰብ ነው።

በአጠቃላይ ሁኔታውን ለማወቅና ለመቃወም ዕድል ባገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከፍተኛ ተቃውሞ የተደረገበትና በኢህአዴግ መንግስት ብቻ ተቀባይነት ያገኘው የሄጉ ውሳኔ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ውሳኔው እንዲሻር የተቀነባበረ ትግል ካላደረግን እስላምቶዳ፣ ዓጋራለ-ኮማ፣ቦሐሎ፣ ካረዳና ሌሎች የምዕራባዊ ቡክናይቲዓረ ሰፊ ለም መንደሮችና ድፍን አድጋዲዓረ የኤርትራ ይሆናሉ ማለት ነው።

የኢህአዴግ መንግስት መልሶ መላልሶ የሄጉን ውሳኔ እንደሚቀበል በተለያየ ሚዲያ ግልጽ ያደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ ላይ ብቻ ከኤርትራ መንግስት ጋር ንግግር እንደሚፈልግ ነግሮናል። ይህ መነጋገር ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ የድንበሩ መስመር ሲሰመር አንዳንድ መንደሮችን ለሁለት የሚከፋፈልበት ሁኔታ ስላለ ይህን ለማስተካከል ብቻ እንደሆነ ጠቅላይ ሚንስተር አቶ መለስ ዜናዊ ደግመው ደጋግመው ነግረውናል። እዚህ ላይ ስለ ሌላው ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትሪያ የተወሰዱት ቦታዎች ብዙ ማለት ባልችልም ከኢሮብ መሬት ወደ ኤርትሪያ የተወሰደው ጠቅላይ ምንስተሩ እንደሚሉት የተወሰኑ መንደሮች ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ ኢሮብን ሙሉ ኢሮብ ከሚያሰኙት መሬቱና ህዝቡ ከአንድ ሶስተኛ መሬትና ህዝብ በላይ እንዳለ ያለ ህዝቡ እውቀትና ፍላጎት ለኤርትሪያ መሰጠቱን ነው። ይህን ሃቅ ሁሉም የኢሮብ ብሄረሰብ አባላትና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ነው። የኢህአደግ መንግስት እስከ ዛሬ በሄጉ ውሳኔ መሰረት ወደ ኤርትራ የተከለለውን መሬታችንና ህዝባችን ለሻዕቢያ ያላስረከበው ይህን ውሳኔ ተግባራዊ ቢያደርግ የኢትዮጵያ ህዝብና ሰራዊት እንደማይቀበለው ስላወቀ ብቻ ነው። ስለዚህ አሁን ይህ የሄጉ ውሳኔ እንዲሻር፣ የኢሮብ መሬትና ህዝብ ከጥንት ከጥዋቱ አባቶቻችን ያቆዩልንን ድንበር ይዞ እንዲቀጥል፣ እኛ ኢሮቦች ኢትዮጵያዊያን እንጂ ኤርትራዊያን እንዳልሆን መንግስታችን በደንብ የሚያውቀው ጉዳይ ቢሆንም በግልጽ ደጋግመን ልንነግረው ይገባናል። ችግራችንን ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያና ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ እንዲያውቁትና ከጎናችን እንዲቆሙም ጥሪ ማስተላለፍ

መቻል አለብን። የኢህአዴግ መንግስት እስከ ዛሬ እንዳደረገው ሁሉ የድንበራችንን ጉዳይ በዝምታና በሽፍንፍን ይዞት እንዲቀጥል ፈጽሞ መፍቀድ የለብንም።

ይህን በዚሁ በማቆም ወደተነሳሁበት ለድንበር ጥበቃ በአከባቢው የሰፈረው ሰራዊት እንዴት ለወጣት ሴቶቻችን መሰደድ ምክንያት እየሆነ እንዳለ ላስቀምጥ። በነገራችን ላይ እኔ ድንበር እንዲጠበቅ የመከላከያ ሰራዊት በኢሮብ መሬት መቀመጥ የለበትም የሚል አቋም እንደሌለኝ ለሁሉም ግልጽ መሆን አለበት። ሰራዊቱ በድንበሩ መቀመጥና ድንበሩንና በአከባቢው የሚኖረውን ህዝብ ከሻዕቢያ ዳግም ወረራ መጠበቅ አለበት በሚለው በሚገባ አምናለሁ። የኔና የበርካት ኢሮብ ተወላጆች ችግር የድንበር ጠባቂ ሰራዊት አሰፋፈርና ከህዝቡ ጋር እንዲኖረው የሚገባ ግኑኙነት በተገቢ ደረጃ በሰራዊትና በአከባቢው ህዝብ መካከል ሊኖር በሚገባው ግልጽ የሆነ ልዩነት ተደርጎለት አለመስፈሩ ላይ ነው። ይህ ግልጽ የሆነ ሰራዊቱ የራሱ ካምፕ ይዞ በካምፑ እንዲኖር ባለመደረጉ፣ ሰራዊቱ ከህዝቡ ጋር በገበሬዎች ቤት አብሮ እንዲኖር ተደርጎ በመቀመጡ፣ አንዳንድ የሰራዊቱ አባላት የአከባቢው ሴቶችን በቀላሉ ለማባለግ አመች ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። እነዚህ ከግል ስሜታቸውና ፍላጎታቸው ውጭ ድርጊቱ በህዝቡ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ በወጣት ሴት እህቶቻችን ላይ የሚፈጥረውን ሞራላዊና አካላዊ ተጽእኖ ምንም የማያገናዝቡ ወታደሮች ድርጊት እህቶቻችንን እንዲሰደዱ እያስገደደ ነው፣ የበርካታ ቤተሰቦች ትዳር እየፈረሰ ነው፣ በርካታ እህቶቻችን ከባህላችን ውጭ ያለ ትዳር እንዲወልዱ እየተገደዱ ነው፣ በርካታዎቹም በዘመን አመጣሹ የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ በሽታ እየተበከሉ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም። ለድንበር ጥበቃ በአከባቢው የተቀመጠ ሰራዊት መማር አለበት በሚል የሰራዊቱ አባላት ከልጆች ጋር አንድ ት/ቤት አብረው እንዲማሩም ተደረጓል። ከነዚህ የሰራዊቱ አባላት አንዳንድ ባለጌዎች ከትምህርት ቤት መልስ ወይም ወደ ት/ቤት ሲመጡ ወጣት ሴቶችን በየሸንጥሮው በመጠበቅ በማታለልና በማስገደድም በመድፈር ላይ ናቸው።

ስለሆነም በዚህ ሁኔታ የተማረሩ ወጣት ሴት እህቶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከዚህ ድርጊት ለመሸሽ ስደትን እንደ አማራጭ እየወሰዱ ነው። አንዳንድ ሁኔታውን የታዘቡና ያወቁ ወላጆችም ልጄ እያየሁ እዚህ በዓይኔ ስር በማትፈልገው ወታደር ከምትደፈር ወደ ፈለገችው ትጥፋ በሚል ልጆቻቸው በጣም አስቸጋሪና አደገኛ የስደት ምረጫ ሁሉ እንዲወስዱ እያዩ ዝም ለማለት የተገደዱበት ሁኔታ ነው ያለው።

ይህ በኢሮብ ዛሬ በወጣት ሴት እህቶቻችንና በአርሶ አደሮቹ ሚስቶች ላይ የሚፈጸመው የአስገድዶ መድፈር በአብዛኛው በአከባቢው በባለስልጣናቱ ሆነ የሃይማኖት መሪዎች በሚገባ ይታወቃል። ነገር ግን ሁሉም ዝምታን መርጧል። ስለሆነም የኢሮብ ወጣቶች በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ ወጣት ሴቶቻችን በወታደሮች ከመደፈር በሚል መሰደድ ቢመርጡም ወደባሰ በሶማሌዎችና በዓረቦች ወደሚደፈሩበት፣ አንዳንዶቹም ውድ ህይወታቸውን ሁሉ ወደሚያጡበት አስከፊ ምርጫ እንዲገቡ እየተደረገ ነው።

ውድ አንባቢያን፣ እንግዲህ እኔ የኢሮብ ወጣቶች መሰረታዊ ችግሮች ናቸው ያልኩዋቸውን ከላይ እንደተመለከታችሁት አስቀምጫለሁ። ጉዳዩ የሁላችን ጉዳይ ስለሆነ እያንዳንዱ/ዷ ያገባኛል፣ የኢሮብ ህዝብ ችግር ችግሬ ነው፣ የሚል/ትል፣ የኢሮብ ወጣቶች ዛሬ ገብተውበት

ያለው እጅግ ከፍተኛ ቀውስ የሚያሳስበው/ባት ችግሩ ሙሉ በሙሉ ከቁጥጥራችን ውጭ ወጥቶ በህልውናችን ላይ ከፍተኛ አደጋ ከማስከተሉ በፊት በአንድነት ይህን ችግር ከስር መሰረቱ ለመቅረፍ ማድረግ ያለብን እናድግር። በሚቀጥለው ይህን የወጣቶቻችን ስደትና ተስፋ መቁረጥ ለማስቀረት ምን ማድረግ አለብን በሚለው በኔ በኩል የሚታዩኝን የመፍትሄ ሃሳቦች ይዤ እቀርባለሁ። በሉ በሚቀጥለው መጣጥፌ እስከምንገናኝ በቸር ሰንብቱ፣ ደግ ደጉን ያሳስበን/ያሰራን አሜን።

ሱመ ነኝ

ጥር 2003 ዓ.ም.